የሰ/መ/ቁ. 77113

ሐምሌ 27 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች**፡- አኪኮ ቦዲዋይዝ ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ አቶ ጌታቸው ወንድሙ ቀርበዋል

**ተጠሪ**፡- አቶ ገረመው አበበ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአሁን አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ህግ በደነገገው መሰረት ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክርና በማስረጃ ከተረጋገጠው የፍሬ ነገር ጉዳይ ጋር በማገናዘብ ለይቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ ሥራዬን በአግባቡ እየተወጣሁ እያለ አሠሪው ወደ ሌላ የሥራ መደብ ተዛውረሃል በአዲሱ የስራ መደብ ሄደህ ሥራ በማለት በቃል ሲገልጽልኝ፣ በተዛወርኩበት ቦታ ሥራዬን በኃላፊነት በአግባቡ እንድወጣ የዝውውር ደብዳቤ ይድረሰኝ በማለት በመጠየቄ በጥበቃ ኃላፊው ተገድጄ እንድወጣ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሣ የሥራ ውሉ የተቋረጠ ስለሆነ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የሚገባኝ ልዩ ልዩ ክፍያ እንደ ህጉ ይፈፀምልኝ በማለት ዳኝነት ስጠይቅ፣ የአሁን አመልካች በበኩሉ ከአሰሪነቱ በመነጨ ሥልጣን ሠራተኛው በሌላ የሥራ መደብ ተዛውሮ እንዲሰራ፣ የዝውውር ደብዳቤ በቀጣይነት እንደሚደርሰው በሥራ ኃላፊው ግልፅ ትዕዛዝ ቢደርሰውም ሥራ አልጀመረም፡፡ በዚህም የተነሳ በቀድሞው የሥራ ቦታ ሊያቆያቸው የሚችል ምክንያት የሌለ መሆኑ ተገልፆ ወደ መደብ የሥራ ቦታቸው እንዲሄዱ ሲነገራቸው ሥራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው ሄደዋል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ የሥራ ውል የተቋረጠው በሠራተኛው ፈቃደኝነት ወይስ በአሰሪው አነሳሽነት? የሚለውን በአከራካሪ ነጥብነት ይዞ በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ሰምቷል፡፡ በተሰማው ማስረጃ መሰረትም አሠሪው ሠራተኛውን የድርጅቱ የሥራ ቦታ በሆነ በሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሰራ በቃል መገለፁንና ሠራተኛውም ዝውውር በፅሁፍ ይድረሰኝ በማለት ሲጠይቅ እንደነበር አሰሪውም በድርጅቱ የጥበቃ ኃላፊ አማካኝነት ሠራተኛው ተገዶ እንዲወጣ ያደረገ መሆኑንና ሠራተኛውም ልብ አድርጉ እያለ ተገዶ ወጥቶ መሄዱን ከዚያም ወደ ሥራ ቦታ ሊመለስ ያልቻለ መሆኑን በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ እንደሆነ ከውሳኔው ግልባጭ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም

አመልካች ሠራተኛው ወደ ተዛወረበት ቦታ አልሄድም በሚል ምክንያት ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቋል የሚለው ክርክሩ በማስረጃው የተረጋገጠውን ጉዳይ መሰረት ያደረገ ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ለግራ ቀኙ ክርክር መነሻ የሆነው የዝውውር ጉዳይ እንደሆነ በማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ ሁለቱንም ወገኖች ያለያያቸው ነጥብ አይደለም፡፡ የተለያዩበት ነጥብ አመልካች እንደ አሰሪነቴ የዝውውር እርምጃውን በቃል ትዕዛዝ አስተላልፌያለሁ፤ በቀጣይም የዝውውር ደብዳቤ እንደሚደርሰው እየተገለፀለት ወደ ምድብ ሥራው መሄድና ሥራ መጀመር ሲገባው ይህንን ሳያደረገም የሚለውን በማስቀደም በሠራተኛው በኩል ጥፋት እንዳለ ለማሳየት ሲል ክርክሩን አቅርቧል፡፡

ይሁን እንጂ ሠራተኛው የተዛወረበት ክፍል ከቦታም ሆነ ከሥራ መደብ አንፃር ሲታይ ቀድሞ ተመድቦ ይሰራበት ከነበረው የሥራ አድራሻም ሆነ የሥራ መደብ የተለየ ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ሲሆን፤ አመልካች ለዚህ ያቀረበው ማስተባበያ ክርክር የለም፡፡ ይህም ከሆነ አሰሪው የዝውውሩን እርምጃ በቃል በማስተላለፍና የሚያስገድድ አጣዳፊ ሁኔታ መኖሩን ካላስረዳ በቀር የዝውውር እርምጃውን በቃል አስተላልፌያለሁ፤ በቀጣይም በደብዳቤ እገልፃለሁ ማለቱ የአስተዳዳሪነት ሥልጣኑን በዘፈቀደ ለማከናወን ከመሻት የመነጨ ምክንያት ነው ከሚባል በቀር የእርምጃውን ህጋዊነት አያሳይም፡፡ ተጠሪም ይህ የዝውውር ውሳኔ በቃል መሆኑ ቀርቶ በፅሁፍ ይደረግልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተዛውሮ እንዲሄድ ከተገለፀለት የሥራ አድራሻ እና የሥራ መደብ አንፃር የአንድ መ/ቤትን አግባብ የሆነ የዝውውር አፈፃፀም ተከትሎ ያቀረበው የመብት ጥያቄ ነው የሚያሰኝ እንጂ የአሰሪውን ትዕዛዝ ላለመፈፀም ያደረገው ተግባር ሆኖ አይገኝም፡፡ በመሆኑም ለግራ ቀኙ ውዝግብ የሆነው ምክንያት አሰሪው በእራሱ በፈፀመው ያልተገባ ተግባር እንደሆነ መረዳት ችለናል፡፡

አሰሪው የወሰድኩት እርምጃ ህጋዊ መሰረት ያለው ነው በሚል ያመነበት ቢሆን እንኳ ተጠሪ ወደ አዲሱ የስራ ቦታ ሄዶ ሥራ ባለመጀመሩ ምክንያት የሥራ ደንቡ እና ህጉ በሚፈቅደው ቅደም ተከተሉ የጠበቀ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰድ ከሚችል በቀር ሠራተኛውን የጥበቃ ኃላፊ በሆነው አማካኝነት ከስራ ቦታ አስገድዶ እንዲወጣ በማድረጉ በእራሱ እጅ የመዳኘት ተግባሩ ሌላው ህጋዊ መሰረት የሌለው እርምጃ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች በሠራተኛው ፈቃድ ሳይሆን ሠራተኛው/የአሁን ተጠሪ/ ደንቡን ባልጠበቀ ዝውውር ምክንያት ለመሄድ እቸገራለሁ በማለት ተገቢው እንዲፈፀም በመጠየቁ ምክንያት አሠሪው ከሥራ ቦታው በድርጅቱ ጥበቃ ሰራተኛ አማካኝነት አስገድዶ በማስወጣቱ ህገ-ወጥ ድርጊት ሆኖ ስለተገኘ የሥር ፍ/ቤቶች ስንብቱ ህጉ ከደነገገው ውጭ የተፈፀመ ነው በሚል የሰጡት ዳኝነት በማስረጃ የተረጋገጠውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች በስንብቱ አግባብነት ዙሪያ ክርክር ከማቅረቡ በፊት በክፍያው ጉዳይ ላይ ያነሳው ክርክርም የለውም፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በበታች ፍ/ቤቶች አመልካች በወሰደው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ሳቢያ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑን ተገንዝበው የሰጡት ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ባለማግኘታችን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በጉዳዩ ላይ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 115625 በ29/3/2004 ዓ.ም የሰጠውና የመጨረሻ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ከዚህ በፊት በዚህ የሰበር መዝገብ ሚያዝያ 13 ቀን 2003 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የተነሳ የደረሰውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/ዘ